# <u>ሰይፉ ነበልባል</u>

# <u>ክርስትና እና ጋዜጠኝነት ሲወሀዱ ወደ ሰይፉ ነበልባልነት ይለወጣሉ።</u>

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@gmail.com

ታሕሳስ ፳፻፰ ዓ.ም.

## *መግቢያ*

*በዚህ ርእስ ይህችን ጦማር እንዳዘጋጅ የተገደድኩበት ምክንያት "የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኔ ለቤተ ክርስቲያኔ እቆማለሁ ፤ ጋዜጠኛ በመሆኔም ለህዝቤ እውነቱን አስጨብጣለሁ" እያሉ፤ ነገር ግን እንደሚሉት ሆነው የማይገኙ እንደ አቶ አዲሱ አበበ የመሳሰሉ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኞች በመካከላችን ስለተከሰቱ ነው። አቶ አዲሱ እንደሚሉት የክርስትና ሕይወትና የጋዜጠኝነት ሙያ የተዋሀዳቸው ቢሆኑ ኖሮ እጅግ በታደልን ነበር። እንደነ ተመስገን ደሳለኝ፣ እስክንድር ነጋና ርዕዮት ዓለሙን የመሳሰሉ ጋዜጠኞች ታስረው በመሰቃየት ላይ ሳሉ፤ በቂ ችሎታና ሙያ ሳይኖራቸው አቅጣጫ እየቀያየሩ በሚፈጽሙት ተደጋጋሚ በደል በአካባቢያችን ያሉትን አብያተ ቤተ ክርስቲያናት ባልወረሩና ወያኔ በሚቆጣጠራቸው መገናኛ አውታሮች ተሰልፈው የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያፈኑ ጋዜጠኞች ቁጥራቸው ባልበዛ ነበር።*

የሚሆነው እየሆነ ነውና፤ <u>የክርስትና እና የጋዜጠኝነ</u>ት ባሕርያት ውህደት አለኝ ብለው በድፍረት ስለተናገሩ፤ በሁለቱ መካከል ያሉትን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማሳየት ወደ ሥረ ነገሩ ከመግባቴ በፊት፤ በዚህ ርእስ ይህችን ጦማር ለመጻፍ ሳስብ በኔ ላይ የሚያስከትለውን ጥያቄ በመዘንጋትና የሚከተለኝን ተቃውሞ ቀላል አድርጌ በመውሰድ አይደለም።

እንኳን ስላልተሰለፍኩበት ጋዜጠኛነት ሙያ፤ ስለተሰለፍኩበት ስለነገረ መለኮት ከዚህ ቀደም ለመጻፍ በጀመርኩበት ጊዜ ግማሹ "ውሸቱን ነው" ሌሎቹ ደግሞ 'መናፍቅ ነው" ለሌሎቹ "ከግል ጥላቻ ነው" ጥቂቶቹ ደግሞ "ሲኖዶሱ የተወውን

ምን አገባው" ይሉ ነበር። ከዚያም ርቀው በቅስናየ ላይ ጥያቄ የነበራቸውም ነበሩ። ከነዚህም አንዱ እራሳቸው ክርስቲያኑ ጋዜጠኛ አቶ አዲሱ ነበሩ።

"ወኢ.ታዕቢ ርዕሰከ በምክረ ነፍስከ፤ ከመ ኢይምስጥዋ ከመ ላህም ለነፍስከ" (ሲራክ 6፡ 2) ። "<u>ፈተና በመጣ ጊዜ መቋቋም ተስኖህ እንደሚነዳ ላም ተሳላቂ እንዳይሳለቅብህ፤ በግብርህ ግለጸው እንጂ ይህን ተማርኩ ይህን አውቃለሁ በማለት ራስህን ከፍ አርገህ አታጉን</u>" የሚለውን ከመተርጉማን ሊቃውንት ብማርም፤ አንዳንድ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዉስጥ የተሰገሰጉ ሰዎች የጻፍኩትን ህዝብ እንዳያነብ እንቅፋት ስለሆኑ፤ መምህሮቼንና የተማርኩባቸውንም መካናት ተገድጄ እንደገለጽኩ፤ "እባብ ያየ በልጥ ደነገጠ" እንዲሉ፤ ዛሬ ደግሞ ስለ ጋዜጠኝነት ስጽፍ፤ ያለ ሙያው በማያውቀው ነገር ባልተሰማራበት ነገር ለምን ይጽፋል? የሚሉ ሰዎች ሊነሱ ይችላሉና፤ እነሱ የሚያሰራጩትን ለመግታት ስለ ክርስቲያን ጋዜጠኛ ሙያ በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ ያለችኝን ትንሽ አቅምና ሙብት ላንባቢ መግለጽ ተገቢ ይመስለኛል።

ከኢትዮጵያ ሊቃውንት የተማርኩትን ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍት፤ ከምዕራቡ አመለካከት ጋራ ማነጻጸር እንድችል የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የሰጠችኝን የነጻ ትምህርት አጠናቅቄአለሁ ። ቤተ ክርስቲያናችን የሰጠችኝን እና ከነሱም የቀሰምኩትን የተመለከቱ እንግሊዞች (Christian journalism & Communication) ባጠና የበለጠ እንደምጠቅም ተገንዝበው ወርልድ ቪዥን ከሚባለው አሜሪካዊው ድርጅት ጋራ በመነጋገር፤ በወርልድ ቪዥን ሞግዚትነት በተሰጠኝ ተጨማሪ የትምህርት እድል፤ ናይሮብ በሚገኘው International Day Star Communication center ይባል በነበረው ትምህርት ቤት ገብቼ ለሁለት ዓመታት ስማር ስለ ጋዜጠኝነት ድርሻና ኃላፊነት ዳስሻለሁ።

የዳሰስኳቸው ሁሉ ሙያዎች "እስከ ትበጽህ ለሞት ተበዓስ በእንተ ጽድቅ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ይትበአስ በእንቲአከ" ( ሲራክ 4 ፡ 28 ) ማለትም:- "እስክትሞት ለእውነት ታገል። እግዚአብሔር ላንተ ይታገልለሀል" ከሚለው ቃል አንዳቸውም ዝንፍ የሚሉ አይደሉም። በነዚህም በሌሎች ሁሉ መስኮች የተሰለፉ ሰዎች ኢትዮጵያንና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያኔን የሚጎዳ ነገር ሲፈጽሙ ተው ለማለት የራሴን ድርሻ እንድወጣ ያደረብኝ የመንፈስ ተጽእኖ እንቅልፍ ይነሳኛል።

ቅዱስ ጳውሎስ "ወዘኒ ዘጸሐፍኩ ለክሙ ከመ መጺእየ ኢይረክበኒ ሐዘን በዘሀለወኒ እትፌሣሀ ተአሚንየ በኩልክሙ ከመ ፍስሐ ዚአየ ዘኩልክሙ ውእቱ። እስመ እምነ ብዙኀ ሕማም ወሀዘነ ልብ ጸሐፍኩ ዘንተ በብዙህ አንብዕ ወአኮ ከመ ትተክዙ ዳእሙ ከመ ታእምሩ አፍቅሮትየ ከመ ፈድፋደ አፈቅረክሙ" (፪ኛ ቆሮ ፪፡፫-፬) እያለ ጻፈ:: ይህም ማለት "ደስታችሁ ደስታየ እንደሆነ ሁላችሁም እንደምትረዱ አምናለሁ። ወደ እናንተ ስመጣ ከመደሰት ይልቅ ሀዘንና ቅሬታ እንዳይገጥመኝ ይህን ጻፍኩላችሁ። ስጽፍላችሁም ልጎዳችሁና ላሳዝናችሁ አይደለም። በብዙ ጥንቃቄ፤ በሀዘን፤ በመጨነቅና በእንባ ነው። ነገር ግን ልመክራችሁና አቅጣጫ ልጠቁማችሁ ነው። ይልቁንም ከልብ እንደምወዳችሁ ተረዱልኝ" እንዳለው፤ <u>እኔም አቶ አዲሱና የመሳሰሉት ክርስቲያን ጋዜጠኞች ነን እያሉ፤ ለተግባራቸው ለእምነታቸው ተስማሚ ስራ እንዲሰሩ፤ መስራት ባይችሉም የተሰለፉበትን ሙያና ድርጅት ለኃጢአት መጋረጃ ቆጽለ በለስ ማድረጋቸውን እንዲያቆሙ ለማሳሰብ እንጂ በጥላቻ ወይም ለመጉዳት አይደለም</u>። በተረፈ የጋዜጠኛነትን ትምህርት ብቀስምም ያልተጠቀሙበት ሙያ፤ በማፋዳው በመታሸጉ ስለቱን እንዳጣ ሰይፍ፤ስላልተጠቀምኩበት ሊዝግ ይችላል። ቢሆንም የሁለቱን ፤ የክርስትንና የጋዜጠኛነትን ግንኙነትና ልዩነት የማሳይበት አቅም ጨርሶ አይጠፋኝምና ከዚህ በታች በዘረዘርኳቸው አንቀጾች በአቶ አዲሱ አበበ አማካይነት ለክርስቲያን ጋዜጠኞች ሁሉ ይህችን ጦማር አቀርባለሁ።

1ኛ፦<u>ክርስቲያንና ጋዜጠኛ</u>

<u>2ኛ፦ክርስትና እና ጋዜጠኝነት ሲወሀዱ</u>

<u>3ኛ፦የናታን ተልእኮ እና የሰሎሞን ሰይፍ</u>

<u>4ኛ፦አቶ አዲሱ በራሳቸው አንደበት የተናገሯቸው ።</u>

# 1ኛ ክርስቲያንና ጋዜጠኛ

**ሀ. ክርስቲያን** ፦ ክርስትና ኩነት (መሆን) እንጂ መመሪያ አይደለም። መመሪያ እንደ ሁኔታው በቦታና በጊዜ የሚቀያየር ነገር ነው። ክርስትና ግን ". . . .ሁሉን ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክቡር ሥጋችንን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል"(ፊል 3፡ 21) እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ፤ ሥጋዊ ምኞታችንንና ፈቃዳችን አስለቅቆ በሰውነታችን የሚተካ ባህርይ ነው። "አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣው መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠብቃለን" (ፊል 3፡ 21) እንዳለውም፤ የክርስቲያኖች ምድራዊ ቆይታ ክርስቶስ ያዘዘውን እየተሰሩ የሚቆዩበት ጊዜያዊ ቦታ እንጅ ዘላለማዊ መኖሪያቸው አይደለም። በምንቆይበት አጭር ዘመናችን፤ በጸሎተ ቅዳሴያችን "በእንተ ሐዋርያት ላእካን ወቅዱሳን ሰማእታት ናስተበቁዕ ከመ እግዚአብኄር የሀበነ ናስምር በከመ እሙንቱ አሥመርዎ ወመከፈልቶሙ ይክፍለነ። የሀበነ ንፈጽም ኪያሆ ግዕዘ" (41; 73) እያልን የምንጸልየው፤ ከክርስቶስ በኋላ ከኛ በፊት የነበሩት ልኡካን፤ እውነትን የመሰከሩባት ተልእኮ በማይረባ ነገር እንዳንሸፍናት የምትረዳን ኃይል እንዳትርቀን ነው።

ምክንያቱም፦ በግል ሞትም ይሁን፡ በክርስቶስ መመለስ፡ የምንኖርባትን ዓለም እስክንለቃት ድረስ ለእውነት ከመመስከር ይልቅ፤ እውነትን አፈር እንድናለብሳት የሚፈትነን ብዙ ነው። ከሞትን በኋላ፡ ነበረ በሚባለው ፈራሽና በሰባሹ ሰውነታችን ውስጥ ነፍስ ተሰውራ እንደምትኖር፤ ክርስቲያናዊት ተልእኮችንም በምልአተ ሀሰት በተጥለቀለቀች ዓለም ውስጥ የተሰወረች በቃላችን በተግባራችን የምትገለጽ ረቂቅ ነፍስ ናት።

ክርስቲያናዊት ተልእኮችን በምልአተ ሀሰት በተጥለቀለቀች ዓለም ውስጥ እውነት ተቀብራ እንዳትቀር፤ ዮሐንስ የሚባለው የእስክንድርያው ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ "ወንሕነሰ ኩልነ እለ ብነ ልብ ክርስቶሳዊ ዘበአማን ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" (ሃ, 90; 38) ማለትም፦ "በእውነት ክርስቶሳዊ ልብ አለን የምንል ከሆነ፤ እውነትን በማግደምደምና አጠይሞ በመናገር ዘመናችንን በከንቱ አናሳልፍ" አለ።

ኤጲፋንዮስ የተባለው ኦርቶዶክርሳዊ ሊቅም "ይእቲ ትሄይስ እምዕንቍ ክቡር ወኩሉ ክብር ኢመጠና፤ ላቲ ምክር ወእዘዝ፤ ወላቲ ጽንዕ ወአዕምሮ፤ ወባቲ ነገሥት ይነግሡ። ወባቲ ኃያላን ይጽህፉ ጽድቀ" (80 ) ማለትም፦ "ክርስቶሳዊት ልብ የማትናወጽ ቀጥ ያለች እውቀት ማስተዋል ፈሊጥ ናት። የሚስተካከላት ዕንቁ ወርቅና አልማዝ የለም። አስተዋይ መሪዎች ህዝባቸውን ይመሩባታል። ኃያላን ጸሐፊዎች ጽድቅን እውነትን ይጽፉባታል" አለ።

ለሁሉ መሰረት በሆነው መጽሐፈ ኦሪት ላይ "አዘዞሙ ለኪሩቤል ወሱራፌል ዘውስተ እደዊሆሙ <u>ሰይፈ እሳት እንተ ትትመየየጥ</u> ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ ዕጸ ሕይወት" ( ዘፍ 3፡24 ) ተብሎ የተነገረውን ማለትም፦ "አዳምና ሄዋን ከዋሹ፤ ከቀጠፉና በቀጠፏት ቅጠል ገበናቸውን በመሸፈን ከገነት ከተባረሩ በኋላ ፤ ተመልሰው እንዳይገቡ የምትገለባበጥ <u>ነበልባላዊት ሰይፈ የጨበጡትን ሱራፌልንና ኪሩቤልን</u> በገነት በር እንዲቆሙ አዘዛቸው" የሚለውን ለ<u>ኃያላን ጸሐፊዎች</u> <u>መግለጫ በማድረግ በሱራፌልና በኪሩቤል ይመስሏቸዋል። ኃያላን የተባሉ የብዕር ሰዎች፤ አገራቸው የቀጠፉ የዋሹ በቆጽለ በለስ እርቃናቸውን የሸፈኑ ሰዎች የሚመላለሱባት የሚኖሩባት እንዳትሆን በየማእዘኑ እየተገለባበጡ ነቅተው የሚጠብቁ ኪሩቤላውያን ይባላሉ። ብዕራቸውም ሰይፈ ነበልባል ትባላለች።</u>

ቅዱስ ቄርሎስም "ወውስተ አርእስተ እሳት እለ ይትለአክዎ"(5) እንዳለው፤ ይህችን ሰይፍ የጨበጡ እሳታውያን ጸሐፊዎች፤ የመለኮትና የህዝባቸው ተላላኪዎች ናቸው። "እለ አቅለሉ ክነፊሆሙ ለተልኢኮ ምሥጢር በዲበ ዛቲ ጠረጴዛ" ጠረጴዛ ህብረተ ሰብ ነው። <u>ተልኢኮ ምሥጢር</u> የተባለችው መለኮት በአምሳሉ የፈጠረው ሰው የሚሳተፋት የተዘረጋች መረብ እውነት ናት። ይህችም የመለኮት ፈቃድ ናት።

ህብረተ ሰብን ለማገልገል የተሰየሙ ክርስቲያን ጋዜጠኞች በጓደኛ፤ ወዳጅ ዘመድ በኩል ባለ ሥልጣናት የጭፏቸውን የጭነት አይነቶች ከላያቸው ላይ የሚያራግፉ፤ የጭነት ማጋዣ መሆንን የተጸየፉ <u>ሰይፈ ነበልባሎች</u> <u>የሞራል ዘበኞች፤</u>

የህዝብ ዲያቆናት መሆን እንዳለባቸው የሚጠቁመውን እስከዚህ ከገለጽኩ፤ ከዚህ ቀጥየ በሙያው ጥልቅና ምጡቅ ችሎታ ያላቸው ጠበብቶች ስለ ጋዜጠኛ ሙያ፤ የሞራል ግዴታና ኃላፊነት የቀረጿቸውን 9 መመሪያዎች እጠቅሳለሁ።

## ለ. ጋዜጠኝነት

Principles of Journalism

The first three years of the Project's work involved listening and talking with journalists and others around the country about what defines the work. What emerged out of thoseconversations are the following nine core principles of journalism:

1. **Journalism's first obligation is to the truth**

Democracy depends on citizens having reliable, accurate facts put in a meaningful context. Journalism does not pursue truth in an absolute or philosophical sense, but it can–and must–pursue it in a practical sense. This "journalistic truth" is a process that begins with the professional discipline of assembling and verifying facts. Then journalists try to convey a fair and reliable account of their meaning, valid for now, subject to further investigation. Journalists should be as transparent as possible about sources and methods so audiences can make their own assessment of the information. Even in a world of expanding voices, accuracy is the foundation upon which everything else is built–context, interpretation, comment, criticism, analysis and debate. The truth, over time, emerges from this forum. As citizens encounter an ever greater flow of data, they have more need–not less–for identifiable sources dedicated to verifying that information and putting it in contex.

**2. Its first loyalty is to citizens**

While news organizations answer to many constituencies, including advertisers and shareholders, the journalists in those organizations must maintain allegiance to citizens and the larger public interest above any other if they are to provide the news without fear or favor. This commitment to citizens first is the basis of a news organization's credibility, the implied covenant that tells the audience the coverage is not slanted for friends or advertisers. Commitment to citizens also means journalism should present a representative picture of all constituent groups in society. Ignoring certain citizens has the effect of disenfranchising them. The theory underlying the modern news industry has been the belief that credibility builds a broad and loyal audience, and that economic success follows in turn. In that regard, the business people in a news organization also must nurture–not exploit–their allegiance to the audience ahead of other considerations.

**3. Its essence is a discipline of verification**

Journalists rely on a professional discipline for verifying information. When the concept of objectivity originally evolved, it did not imply that journalists are free of bias. It called, rather, for a consistent method of testing information–a transparent approach to evidence–precisely so that personal and cultural biases would not undermine the accuracy of their work. The method is objective, not the journalist. Seeking out multiple witnesses, disclosing as much as possible about sources, or asking various sides for comment, all signal such standards. This discipline of verification is what separates journalism from other modes of communication, such as propaganda, fiction or entertainment. But the need for professional method is not always fully recognized or refined. While journalism has developed various

techniques for determining facts, for instance, it has done less to develop a system for testing the reliability of journalistic interpretation.

**4. Its practitioners must maintain an independence from those they cover**

Independence is an underlying requirement of journalism, a cornerstone of its reliability. Independence of spirit and mind, rather than neutrality, is the principle journalists must keep in focus. While editorialists and commentators are not neutral, the source of their credibility is still their accuracy, intellectual fairness and ability to inform–not their devotion to a certain group or outcome. In our independence, however, we must avoid any tendency to stray into arrogance, elitism, isolation or nihilism.

**5. It must serve as an independent monitor of power**

Journalism has an unusual capacity to serve as watchdog over those whose power and position most affect citizens. The Founders recognized this to be a rampart against despotism when they ensured an independent press; courts have affirmed it; citizens rely on it. As journalists, we have an obligation to protect this watchdog freedom by not demeaning it in frivolous use or exploiting it for commercial gain.

**6. It must provide a forum for public criticism and compromise**

The news media are the common carriers of public discussion, and this responsibility forms a basis for our special privileges. This discussion serves society best when it is informed by facts rather than prejudice and supposition. It also should strive to fairly represent the varied viewpoints and interests in society, and to place them in context rather than highlight only the conflicting fringes of debate. Accuracy and truthfulness require that as framers of the public discussion we not neglect the points of common ground where problem solving occurs.

**7. It must strive to make the significant interesting and relevant**

Journalism is storytelling with a purpose. It should do more than gather an audience or catalogue the important. For its own survival, it must balance what readers know they want with what they cannot anticipate but need. In short, it must strive to make the significant interesting and relevant. The effectiveness of a piece of journalism is measured both by how much a work engages its audience and enlightens it. This means journalists must continually ask what information has most value to citizens and in what form. While journalism should reach beyond such topics as government and public safety, a journalism overwhelmed by trivia and false significance ultimately engenders a trivial society.

**8. It must keep the news comprehensive and proportional**

Keeping news in proportion and not leaving important things out are also cornerstones of truthfulness. Journalism is a form of cartography: it creates a map for citizens to navigate society. Inflating events for sensation, neglecting others, stereotyping or being disproportionately negative all make a less reliable map. The map also should include news of all our communities, not just those with attractive demographics. This is best achieved by newsrooms with a diversity of backgrounds and perspectives. The map is only an analogy; proportion and comprehensiveness are subjective, yet their elusiveness does not lessen their significance.

**9. Its practitioners must be allowed to exercise their personal conscience**

Every journalist must have a personal sense of ethics and responsibility–a moral compass. Each of us must be willing, if fairness and accuracy require, to voice differences with our colleagues, whether in the newsroom or the executive suite. News organizations do well to nurture this independence by

encouraging individuals to speak their minds. This stimulates the intellectual diversity necessary to understand and accurately cover an increasingly diverse society. It is this diversity of minds and voices, not just numbers, that matters. http://www.journalism.org/resources/principles-of-journalism/

ከዚህ በላይ ስለ ክርስቲያን ጋዜጠኛ የገለጽኩትን እና፤ በጋዜጠኝነት ሙያ ጥልቅና ምጡቅ ችሎታ ያላቸው ጠበብቶች፤ ጋዜጠኛ ያለበትን የሞራል ግዴታና ኃላፊነት የሚገልጹትን ከ 1 እስከ 9 የዘረዘሯቸውን መመሪያዎች ሳንረሳ፤ አቶ አዲሱ አበበ የዋሽንግቶን ዲሲ ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንን ለመክሰስ ለሰበሰቡት ህዝብ ባቀረቡት ውይይት ላይ፤ "ለኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ባህሌ ቋንቋየ እምነቴና ኢትዮጵያዊነቴ ነች። በሥራየ ጠባይ እውነት እንዳይሸፈን የሰው መብት እንዳይረገጥ የምፍጨረጨር ስሆን፤ አጠገቤ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ በደል ሲፈጸም ለህዝብ መናገር አለብኝ" ብለው እራሳቸው በተናገሩት ስንመዝናቸው ፤ ክርስቲያን ጋዜጠኝነት በህይወታቸው የተወሀደላቸው ቢሆኑ ኖሮ፤ ልክ የማይገኝላቸው ሰይፈ ነበልባላዊ ጋዜጠኛ መሆን ይችሉ እንደነበር ለማሳየት፤ የክርስትናን እና የጋዜጠኛነት ውህደት ከዚህ በታች እንመልከት።

## 2ኛ፦ክርስትና እና ጋዜጠኝነት ሲወሀዱ

የክርስትናና የጋዜጠኝነት ሊቃውንት እንደሚያስቀምጡት "የክርስትና እና የጀርናሊዝም ውህደት በሰዎች ላይ ሲከሰት ብልጭ ብሎ የማይጠፋ ፤ ህዝቡን ተብትቦ ያሰረውን ማእሰረ ፍዳ ለመበጣጠስ እንደ መብረቅ የተንቀለቀለ ሰይፈ ነበልባል ቦግ ይላል" ይሉና፤ ከውስጣቸው የሚፈልቀውን የውህደት ኃይል መግለጽ የሚችል የቋንቋ ቃላት ስለሚያጥር "መቃተት ነው" ይላሉ። ይህም ማለት ክርስትናና እና ጋዜጠኝነት የተወሀደላቸው ጋዜጠኞች ለሚያገለግሉት ህዝብ የሚጽሟቸው ተግባራት እጅግ እጹብ ድንቅ ተአምር ይሆናሉ ማለት ነው። መገዛት በኃጢአት ውርስ በሰው ላይ የመጣ ስለሆነ ለሮማው መንግሥት ወግኖ ተገዙ እያለ አውግስቲን ሲሰብክ፤ ቅዱስ ዮሐንስ ከህዝቡ ጎን ተሰልፎ አውግስቲንን በገሰጸበት ህዝቡን እያስተማረ በመራበት ወቅት፤ በዮሐንስ እንቅስቃሴ የረካውን ህዝብ፤ ቅዱስ ዮሐንስን "አፈወርቅ" ነህ እንዳሰኘው ማለት ነው።

ክርስቲያን እውነትን በኃጢአት ተሸፍና ሲያገኛት፤ ከተሸፈነችበት ሽፋን (ኃጢአት ) ገልጦ ለማቅረብ እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚያደርገው ጥረት፤ ኃጢአት እንዳይበክለው ተጠንቅቆ እውነትን ለይቶ ለማቅረብ ይጥራል እንጅ፤ ሆን ብሎ የሰው ኃጢአት እየቆፈረ አያወጣም። ጋዜጠኛ ግን ኃጢአትን አሳዶ፤ አባሮ፤ አድኖና አሽትቶ ለማውጣት የሰለጠነበት ግዴታውና ኃላፊነቱ ነው። ስለዚህ ክርስትና እና ጋዜጠኝነት የተወሀዱለት ሰይፈ ነበልባላዊ ጋዜጠኛ ለመሆን እጽፍ ድርብ ሐላፊነትና ግዴታ አለበት። ይህን እጽፍ ድርብ ኃላፊነት መግለጽ ይችላሉ ብየ የገመትኳቸውን የናታንን ተልእኮ እና የሰሎሞንን ሰይፍ ባጭሩ ገልጬ፤ ለዚህ ጽሑፍ መነሻ ወደ ሆኑኝ ወደ አቶ አዲሱ አበበ እሻገራለሁ።

## 3ኛ፦የናታን ተልእኮ እና የሰሎሞን ሰይፍ

ሀ. የናታን ተልእኮ፦"ወፈነዎ እግዚአብሔር ለናታን ኀበ ዳዊት"(2 ሳሙ 12፡1 )። ናታን የተደበቀውን አሳዶ ለማውጣት እንደ ሰለጠነ የፖሊስ አነፍናፊ ዉሻ (canine dog) ዳዊትን አንቆ ያዘው። ዳዊት ኦርዮንን በግፍ ካስገደለ በኋላ፡ የኦርዮንን ሚስት ለራሱ ወሰደ። ኦርዮን እንዴት እንደሞተና ማን እንዳስገደለው ከህዝብ ድብቅ ነበር።

ነቢዩ ናታን፤ ኦርዮንን ወርቅ፡ ባለበጉን ሰም፤ የኦርዮንን ሚስት ወርቅ፣ በጊቱን ሰም፤ አንድን ስስታም ሁብታም ሰም፡ ዳዊትን ወርቅ አድርጎ; በራሱ በዳዊት ፊት ቅኔውን ዘረፈ። በደም የተነከረው ዳዊት በሌላ ሰው ላይ የተነገረ መስሎት "እጅግ ተቆጥቶ ይህን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው" (5) አለና ስልጣኑን ሽፋንና ተገን አርጎ በፍርድ ላይ መቀለድ ጀመረ።

ነቢዩ ናታን ንጉሥ ዳዊትን ሳይፈራ “ኦርዮንን በሰይፍ መትተህል ሚስቱንም ወስደህል እርሱንም በአሞን ሰይፍ ገድለህልና ለዘላለም ከቤትህ ሰይፍ አይርቅም” በማለት ተልእኮውን ወደ ምትገለባበጥ ሰይፈ ነበልባልነት ለወጣት። “ያ ሰው አንተ ነህ” ብሎም ዳዊትን አንቆ ያዘው። የናታን ተልእኮ እንደ ኪሩባል ነበልባላዊት ሰይፍ በመገለባበጥ ዳዊትን ማምለጫ ቀዳዳ አሳጣችው። ዳዊት ሥልጣኑን በመንተራስ ከገባበት ማነቆ እራሱን አውጥቶ፤ ነፋስ የሚጎስም የከሸፈና ዓላማውን የሳተ ፍርድ ፈረደ። ዳዊት አቅጣጫ ቀይሮ የሰነዘረውን የከሸፈ ፍርድ፤ ናታን አስተካክሎ በራሱ በዳዊት ላይ ገለበጠበት። የናታን ተልእኮ ዳዊትን “እግዚአብሔርን በድያለሁ” ብሎ በመጸጸት ከተሳሳተ ሰውነት ወደ ተስተካከል ሰውነት ገለበጠችው። ናታንም በነበልባላዊት ተልእኮው ዳዊትን አንቆ ከያዘው በኋላ “እግዚአብሔር ኃጢአትህን አርቆልህል አትሞትም” በማለት አጽናናው። እምነት ያለው ጋዜጠኛ እንደ ናታን፤ በደለኛውን ከበደሉ የሚያላቅቅ ነበልባላዊ ሰይፍ መሆን አለበት።

ለ. የሰሎሞን ሰይፍ፦ ውሸትን፣ ቅጥፈትን ቆርጣ የምትጥል በኪሩቤል እጅ ላይ የነበረችውን ነበልባላዊት የእሳት ሰይፍ የምታስታውስ ነበረች። የራሷን ልጅ ገድላ፤ የሌላዋን ልጅ ለማስገደል በተሰለፈችው በሀሰተኛዋና ባስመሳይዋ እናት ነኝ ባይዋ እና፤ በእውነተኛዋ እናት መካከል የተፈጠረውን ውስብስብ በጣጥሶ እውነትን ከተደበቀችበት ፈልፍሎ ለማውጣት ሰሎሞን የተጠቀመባት የምትገለባበጥ ሰይፈ ነበልባል ነበረች። ክርስትና እና ጋዜጠኝነት የተወሀደው ጋዜጠኛ እንደ ሰሎሞን እናትንና ልጅን የሚያገናኝ፤ ሀሰትንና ማስመሰልን የሚያስወግድ ሰይፈ ነበልባል ይሆናል። አቶ አዲሱ አበበ እስካሁን በየ አንቀጾች በተገለጹት መስፈርቶች ሲመዝኑ፤ ሚናውን የጠበቀ ጋዜጠኛ እንደሚያደርገው፤ ራሱን እንደ ሰለጠነ አነፍናፊ የፖሊስ ዉሻ (canine dog) አድርጎ፤ የተደበቀውን ቅጥፈት፤ ሀሰት፤ ሽፍጥ አሳደው ለህዝብ ማቅረባቸው ይቅርና ገንፍሎ በመፈንዳት በሩቅ እንደ ሚታይ ተራራ ሆኖ ሊደበቅ የማይቻለውን የጓደኞቻቸው ስህተት ለመጋረድ፤ ለመሸፈንና ለማፈን የሞከሩ መሆናቸውን እንደሚከተው እገልጻለሁ

## 4ኛ፦ አቶ አዲሱ በራሳቸው አንደበት የተናገሯቸው ።

- 1ኛ፦”ለኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባህሌ ቋንቋየ እምነቴና ኢትዮጵያዊነቴ ነች“
- 2ኛ፦“እዚህ ጥቂት ሰዎች እየፈራን ሌላውን የመጻፍ የመናገር መብት ገድበህል ለማለት ምን አይነት የሞራል ብቃት አለን?”
- 3ኛ፦“የሰው መብት የሚረግጥ ሰው፤ ለኔ በጣም ከሰውነት ባህርይ ያነሰ። ሰው ያልሆነ ሰው ነው”
- 4ኛ፦“ለቤተ ክርስቲያን ቀራቢ እንደመሆኔ በግሌ ባለኝ ፍላጎት እንጅ VOA ልኮኝ አይደለም። እንደ ጋዜጠኛነቴ አድማጭ መረጃ ማግኘት አለበት ብየ ስለማምን የማውቀውን ነገር ለማካፈል ነው የተገኘሁት። የኔ ሚና ይህ ነው።”

አቶ አዲሱ አበበ ከ 1 እስከ 4 የተዘረዘሩትን ከፈጸሙ፤ ክርስትናን እና ጋዜጠኝነትን አዋህደው የተሰለፉ ሰይፈ ነበልባል ክርስቲያን ጋዜጠኛ ናቸው ማለት ነው። ። ግን እሳቸው እንዳሉት ሆነዋልን? እንመልከት!

ለምሳሌ የካቲት 7 ቀ ን 20004 ዓ.ም አሪዞና ፊኒክስ ላይ በተካሄደው የሲኖዶስ የእርቅ ጉባዔ ላይ፤ አቶ አዲሱ ተገኝተው ነበር። የVOA ባልደረባ አቶ ሶሎሞን ስለ ሚካሄደው ጉባዔ ለህዝብ ለማቅረብ ፈልገው፤ አቶ አዲሱን “በሽምግልናው አለህበት ይባላል ለመሆኑ ያንተ ሚና ምንድነው? ብለው ለጠየቋቸው፤ አቶ አዲሱ የሰጡት መልስ፤ *“ለቤተ ክርስቲያን ቀራቢ እንደመሆኔ በግሌ ባለኝ ፍላጎት እንጅ VOA ልኮኝ አይደለም። እንደ ጋዜጠኛነቴ አድማጭ መረጃ ማግኘት አለበት ብየ ስለማምን የማውቀውን ነገር ለማካፈል ነው የተገኘሁት። የኔ ሚና ይህ ነው።”* የሚል ነበር። [ የአሜሪካ ራድዮ ድምጽ የቀረበውን ሙሉውን ቃለ-መጠይቅ ለማዳመጥ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ። አዲሱ አበበ ሁለቱን የሲኖዶስ ወገኖች ለማስታረቅ ፊኒክስ አሪዞና በመገኘት የሰጡት ዘገባ]

*“ለቤተ ክርስቲያን ቀራቢ እንደመሆኔ በግሌ ባለኝ ፍላጎት እንጅ VOA ልኮኝ አይደለም”* ብለው አቶ አዲሱ የተናገሩትን ስንመለከት፣ ቤተ ክርስቲያናችንን በተመለከተ ሲሰሩት የኖሩት በግላቸው ፍላጎትና ለቤተ ክርስቲያን ቀራቢ ስለሆኑ እንጅ VOA እየላካቸው አልነበረም ማለት ነው። እንደገባኝ ከሆነ፤ ይህ ንግግራቸው ባልደረቦቻቸው ኢትዮጵያውያን፤ አቶ አዲሱን እሁድ እሁድ እየጠመጠሙ መቋሚያ እየወዘወዙ በቤተ ክርስቲያን ስለሚያዩዋቸው ለቤተ ክርስቲያን ቀራቢ ናቸው ብለው በማመን

የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ያለ አንዳች ገደብ አምነው ለቀውላቸዋል። ይህን በእምነት የተሰጣቸውን የጋዜጠኝነት ኃላፊነት ካልተወጡ *“እንደ ጋዜጠኛነቴ አድማጭ መረጃ ማግኘት አለበት ብየ ስለማምን የማውቀውን ነገር ለማካፈል ነው የተገኘሁት” ያሉትን አቶ አዲሱ ክደዋል። “የኔ ሚና ይህ ነው”* ያሉትንም ረስተዋል::

አቶ አዲሱ ባንድ በኩል ይህን እየተናገሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአባ ፋኑዔልና በታደሰ ሲሳይ የተከሰተውን ጉዳይ እያወቁና እያዩ ለምን አፈኑት ሲባሉ፤ የነገሩን ክብደት ሳይሸፍኑ “ለፕሮግራም የሚሆን ነገር አይደለም። VOA የራሱ አሰራር አለው” ብለው በሰጡት መልስ፤ ወዳጆቻቸውን ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ፤ የክርስትናቸውን እና የጋዜጠኛነታቸውን የሞራል ግዴታ ገደል ከተቱት። VOA ንንም የራሳቸው ደካማ አላማ መጋረጃ አድርገውታል። ኢትዮጵያውያንንም ከተወልድንባት ከኢትዮጵያ ይልቅ የተሻለ ኑሮ የምንኖርባትን የምንወዳትን አሜሪካን እንድንጠላ ያደረጉት ሙከራ ሌላው ስህተታቸው ነው። በ VOA ተቀጥረው ለሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያን ባልደረቦቻቸውም ታላቅ ሀፍረት ይመስለኛል። [*በታደሰ ሲሣይና በአባ ፋኑኤል የተነሳውን ጉዳይ በዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ! በአባ ፋኑኤል ላይ የተሰጠ *መግለጫ -በዓለም የሚሰራጭ::*]

አቶ አዲሱ አበበ በዋሺንግቶን ዲሲ በምትገኘውን የደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የሰበካ ጉባኤ (ቦርድ) ጋራ ያላቸውን ግጭት ለተሰበሰበው ህዝብ በአብሲኒያ ሬድዮ (በአቶ አያልቅበት ራዲዮ) ቀርበው ሲገልጡ:- “እኔ በዚህ አገር በኖርኩበት ዘመን በዚህ አገር ራዲዮን ተናግሬ አላውቅም። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያኔ ላይ የማልፈልገውን ርእስ ይዥ እንድነሳ ተገድጀ እንድናገር ስለተገደድኩ እጅግ አዝናለሁ። መጥፎ አጋጣሚ ነው። በሥራየ ጠባይ እውነት እንዳይሸፈን የሰው መብት እንዳይረገጥ የምፍጨረጨር ስሆን፤ አጠገቤ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ በደል ሲፈጸም ለህዝብ መናገር አለብኝ” ብለዋል። [*በዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያዳምጡ።* አዲሱ አበበ በዋሺንግቶን ዲሲ በምትገኘውን የደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የገባበትን ግጭት ለመቀስቀስ ከአቶ አያልቅበት ሬድዮ ጋር ያደረጉት ቃለ-መጠይቅ ]

ታዲያ ይህንን እያሉ ለክርስትናቸውና ለሙያቸው ያላቸውን ታማኝነት ሲያረጋግጡ “በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የተካሄደውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ይህም ጉዳይ ለፓትርያርኩ ለአቡነ ማትያስ ባቀረብንላቸው ጊዜ አልቅሰው ወዲያውኑ መልስ እንደሚሰጡን ቃል ገብተው እንደሄዱ በመካከል ስለ ነበርክ አይተሀል። ይህን እስከ ዛሬ አፍነህ ይዘህ፤ እንዴት ዛሬ ለሙያህና ለእምነትህ ተቆርቋሪ መስለህ ቀረብክ? ብለው መጠየቅ የሚችሉ ብሩህ፤ የሚያስታወስ ጭንቅላት ያላቸው፤ የተማሩና የሞራል ሰዎች በኢትዮጵያውያን መካከል መኖራቸውን መርሳታቸው ብቻ ከሚመኩበት ሙያቸው መውደቃቸውን ያረጋግጣል።

የጋዜጠኛ ሙያቸውን ለግል ስሜታቸው መጠቀሚያ በማድረጋቸውና የሞራል ግዴታቸውን በመርሳታቸው በመታዘብ ያዝኑባቸው ከነበሩት ሰዎች መካከል፤ እራሳቸው አቶ አዲሱ የሰበሰቡትን ጉባዔ እንደ እድል ተጠቅመው ፤ “እስከዚህች ቅጽበት ድረስ ይህን ሁሉ አፍነህ ይዘህ አሁን “በሥራየ ጠባይ እውነት እንዳይሸፈን የሰው መብት እንዳይረገጥ የምፍጨረጨር ስሆን፤ አጠገቤ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ በደል ሲፈጸም ለህዝብ መናገር አለብኝ” እንዴት ማለት ቻልክ የሚል ጥያቄ አቀርቡላቸው፤ አቶ አዲሱ የሰጡት መልስ “እነሱ ለፓትርያርኩ ክስ ባቀረቡ ጊዜ ተገኝቼ ነበር። ለፕሮግራም የሚሆን ነገር አይደለም። VOA የራሱ አሰራር አለው” የሚል ነበር። [*በዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን አቶ አዲሱ የተናገሩትን ያዳምጡ።* አዲሱ አበበ በደረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ላይ ችግር አለ ብለው ራስቸው በጠሩት ስብሰባ ላይ የተናገሩት ]

አቶ አዲሱ የቅድስት ማርያም ቦርድ ስህተት ፈጸመ ብለው “ሰማይ ተናደ መሬት ተናወጸ” እያሉ ከተማውን ያናወጹበት ህዝቡን ያሸበሩበት ጉዳይ ይከፋል? ወይስ እነ አባ ፋኑዔል ከህዝቡ በሰበሰቡት ሙዳየ ምጽዋት ወታደር እየቀጠሩ ምእመናን ማባረርና በሚሊዮን የሚቆጠር የካሳ ብር ከምእመናን ለመቀበል መክሰስ? ያካባቢውን ወታደሮችና ዳኞችች ማሰልቸት፤ ታላቋን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ማስነቀፍ፤ ቅስናውን ምንኩስናውን ይህን ከመሰለ ነውር ላይ መጣል? ቁምስናን ለከፋ ተግባር መሸፈኛ አድርጎ ማቅረብ? የትኛው ይከፋል? የትኛው ነው ባካባቢው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን የሚያምሰው ? የክርስቲያን ጋዜጠኛን ሚና እንዲገባበት በጽኑ የሚጠይቀው የትኛው ነው? በዚህ ጉዳይ ላይ

በተደረገው ስብሰባ ስላልተለዩ ይህን ሁሉ ትርምስ ከሚፈጽሙት ሰዎች ጋራ ህብረት የላቸውም ማለት ይቻላልን? "ለፕሮግራም የሚሆን ነገር አይደለም። VOA የራሱ አሰራር አለው" ማለትስ እንዴት ይችላሉ? [ *በታደሰ ሲሣይና በአባ ፋኑኤል የተነሳውን ጉዳይ በዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ! በአባ ፋኑኤል ላይ የተሰጠ መግለጫ -በዓለም የሚሰራጭ::]

እውነት አቶ አዲሱ አበበ እንደሚሉት በነ አባ ፋኑዔል የተፈጠረው ቀውስ ለፕሮግራም የሚሆን አይደለም ? አቶ አዲሱ የሚፈልጉትን ሀሳብ ህዝብ እንዲደግፍላቸው የህዝቡን አቋም ለማስቀየር ሲፈልጉ ጥቂትም ብትሆን በየ አጋጣሚዋ በአሽሙርና አጋድሞ በማቅረብ የማያደርጉት ሙከራ የለም። ለምሳሌ አምና ስለ ጥምቀት በዓል አውስተው ከባልደረባቸው ጋራ ሲነጋገሩ "መሪዎች ወደ ትክክለኛ ህሊና እስኪመጡ ድረስ የትም ባለመሄድ ምእመናን እንደኔ አቋም ቢወስዱ ይሻላቸዋል"በማለት ህዝቡ የግላቸውን አቋም እንዲከተል VOA ን ተጠቅመዋል። [*አቶ አዲሱ በአሜሪካ ድምጽ ያስተላለፉትን የህዝባዊ እምቢተኝነት ጥሪ ለማዳመጥ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያዳምጡ።* አቶ አዲሱ አበበ የጥምቀት በዓል አድማ ጥሪ]

በዚህም ብዙ ህዝብ ቅር ብሎት ተተችተውበታል። [*በአቶ አዲሱን ላይ ከቀረቡት የህዝቡ ቅሬታዎች አንዱን ለማዳመጥ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያዳምጡ።* የአሜሪካ ሬድዮ ድምፅ አድማጭ ያሰሙት የቅሬታ መልዕክት ]

*ታዲያ እሳቸው እንደነገሩን ይህ ሁሉ የ VOA አሰራር ነው ብለን በመቀበል ከ voa ጋራ መጋጨት አለብን? ይህን እንኳን የሚያስተውል የለም ብለው ማሰባቸው ህዝብን መናቅና በወገን መቀለድ አይደለምን? ለመሆኑ የቱ ጉዳይ ነው የሚከብደው? ከተማውን ያናገው? ያሜሪካን ወታደር ያሰለቼው? ፍርድ ቤቱም ከባህል ከሃይማኖት ጋራ በመቆላለፉ ለመወሰን ያስቸገረው? ለእምነቱና ለባህሉ የሚያስበውን ህዝበ ክርስቲያኑን አንገት ያስደፋው? ወይስ የጥምቀትን በአል በአባ ፋኑዔል ቡራኬ አለማክበር? ወይስ አባ ፋኑኤል የቤተክርስትያናችንን ዶግማ የጣሰውንና ስለእምነታቸውንና ስለቤተክርስቲያናቸው የሚታገሉትን ምእመናንን ከቤተክርስቲያን በፓሊስና በሴኩሪት የሚያባርረውን ግለ ሰብ ቆሞስ እያደረጉ በህዝብ ላይ መልቀቅ? በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመው ስህተት ያካባቢው ህዝብ እንደሚውቀው ዓለም አቀፍና ብሄራዊ የሆነ ነገር ነው።*

*ቤተ ክርስቲያኗ የተመሰረተችው ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ እንግዶች የሚያርፉባቸው ሆቴሎች፤ የንግድ እና የባህል ማእከሎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፤ ከዚያም በተጨማሪ የኢሳት ጋዜጠኞች በሰፈሩበት ቦታ ነው። ችግሩ ከተከሰተ ጀምሮ ምእመናኑ በየሳምንቱ እሁድ እየጮሁ ናቸው። የውጭ ሰዎች እየተመለከቱ ምንድናቸው? ከየት ናቸው? ለምን ይጮሀሉ? ቤተ ክርስቲያኒቱ ተመልካች የላትም? የሚለው ጥያቄ እየተነሳ ነው። ህዝቡም እየታመሰ ነው። የክፍሉ ጳጳሳ ነኝ የሚሉት የአቶ አዲሱ አበበ ጓደኛ አባ ፋኑኤል ሲጠየቁ "በእናት ቤተ ክርስቲያን ስር አይደለም። ጥርስ የሌለው አንበሳ ነኝ" ከማለት በቀር የተነሳውን ተቃውሞ በሽምግልና ለማብረድ እንኳ አልሞከሩም። አቶ አዲሱ "ለኔ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋየ ባህሌ እምነቴ ናት" ብለው ለሚናገሩላትና ቤተ ክርስቲያናቸውና፤ ሚናየ ነው ብለው ለሚመኩበት ጋዜጠኛነታቸው ምን አደረጉ? እንዲያውም ለጓደኞቻቸው ሽፋን ለመስጠት በሚያደርጉት ጥረት፤ መገለጽ የሚገባውን አፍነው በመያዝ ቤተ ክርስቲያናችንን እና ሙያቸውን እጅግ እየጎዱ ናቸው።*

*በአቶ አያልቅበት ራዲዮ እንደሰማነው፤ አቶ አዲሱ በመሩት ጉባዔ ላይ ጉዳዩ ተነስቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ አቶ አዲሱ ሲመልሱ "እባካችሁ እንዲህ አታድርጉ ስላቸው እምቢ አሉ" እያሉ እነ አባ ፋኑዔልን እየወቀሱና እየከሰሱ ሲናገሩ፤ እስከ ያዚያች ቅጽበት ድረስ አፍነው መያዛቸውን ከመግለጻቸው ባሻገር "እንዲያውም ይባስ ብለው ወደ ቁምስና መሻገራቸው የባሰ ስህተት ፈጸሙ" ማለታቸው፤ ወዳጆቻቸው እጽፍ ድርብ በደል በመፈጸም ላይ እንዳሉ መሰከረዋል። ይሁን እንጅ ከመጀመሪያ ጀምሮ ወጆቻቸው የሚፈጽሙትን ደባ ህሊናቸው ቢያውቅም፤ አፍነው ያዙት እንጅ መቼ ተናገሩ? ታዲያ "በሥራየ ጠባይ እውነት እንዳይሸፈን የሰው መብት እንዳይረገጥ የምፍጨረጨር ስሆን፤ አጠገቤ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ በደል ሲፈጸም ለህዝብ መናገር አለብኝ" ማለታቸው ተገቢ ነውን?*

እነ አባ ፋኑኤል በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት የፈጽሙት ህውከት እራሳቸው አቶ አዲሱ በሽማግልና እንዲቆም፤ ህዝቡ ተሰብስቦ ባደረገው ሙከራ፤ ወደ ተወቃሹ ግለ ሰብ የተላከው የሽምግልና ቡድን የተወቃሹን ወላጅ እናት አግኝቶ ከሽምግልናው ገብተው ልጃቸውን መክረው በመመለስ በእርቅ እንዲፈጸም ሽምግልናውን እንዲቀላቀሉ ሲጠየቁ፤ አቶ አዲሱ ነበሩ።

ታደሰ ሲሳይ ንስሀ እንዲገቡ የጠየቋቸውን ምእመናን ከህዝቡ በሰበሰቡት ገንዘብ ዘበኛ እየቀጠሩ ህዝቡን ሲያባርሩ ያያሉ። ህዝቡንም በሚሊዮን ዶላር ካሳ ሲከሱና ለፖሊስና ለማሪካ ባለ ስልጣናት አሰልቺ እንደሆነ ያውቃሉ። በዚህ ሁሉ ምክንያት በቀጠለው ስብሰባ ውግዘቱን ስናካሂድ በመካከላችን ነበሩ። አቶ አዲሱ አበበ በቤተ ክርስቲያናችን ህግ ውግዘቱን ካልተቀበሉ ከዚያው ላይ ውግዘቱ ትክክል አይደለም ብለው መቃወም የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ነበር። ከሁለት ሰዎች በላይ በበቂ ማስረጃ ደጋፊ ካገኙ ውግዘቱ ቆሞ እንደገና ጉዳዩ እንዲመረምር በተደረገ ናበር። እሳቸው ግን ውግዘቱን ከህዝብ ጋራ ተባብረው ፈጽመው ሄደዋል። [አቶ አዲሱ አበበ ቀኖና ፈሯል ብለው የተናገሩትን *በዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያዳምጡ።* [አዲሱ አበበ በደረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ላይ ችግር አለ ብለው ራስቸው በጠሩት ስብሰባ ላይ የተናገሩት ]]

“በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የተካሄደውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ይህም ጉዳይ ለፓትርያርኩ ለአቡነ ማትያስ ባቀረብንላቸው ጊዜ አልቅሰው ወዲያውኑ መልስ እንደሚሰጡን ቃል ገብተው እንደሄዱ በመካከል ስለ ነበርክ አይተሀል። ያን ሁሉ አፍነህ ይዘህ አሁን “በሥራየ ጠባይ እውነት እንዳይሸፈን የሰው መብት እንዳይረገጥ የምፍጨረጨር ስሆን፤ አጠገቤ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ በደል ሲፈጸም ለህዝብ መናገር አለብኝ” እንዴት ማለት ቻልክ? በሚል ጥይቄ ተጣብቀው ሲያዙ “እንደ ጋዜጠኛ ሆኘ በመንግሥት የተመረጡት ፓትርያርክ በመጡ ጊዜ ላናግራቸው ፈልጌ ነበር። እንደምጠረጥረው ካሁን በኋላ አዲሱን እንዳያነጋግሩት ተብለው ይመስለኛል በግሌ ወይም በአባ ፋኑዔል በኩል ሄጄ መጠይቅ ላቀርብላቸው ሞክሬ እምቢ አሉኝ” ብለው አቡነ ማትያስን ለመውቀስ ሞከሩ።

በመሰረቱ አቶ አዲሱ ክርስቲያን ጋዜጠኛ ቢሆኑ ኖሮ “እንደምጠረጥረው ካሁን በኋላ አዲሱን እንዳያነጋግሩት ተብለው ይመስለኛል” በማለት ከጥርጥና ከመሰለኝ ያልጸዳ ሀሳብ ያውም ግለ ሰቡ በሌሉበት ለህዝብ አያቀርቡትም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ አቡነ ማትያስ በሌሉበት አቶ አዲሱ የተናገሩትን ላይቀበሉትም ይችሉ ነበር። አቶ አዲሱ አቡነ ማትያስን እንዲጠይቋቸው ያስገደዳቸው ምክንያት፤ እሳቸው የሚያውቁት ከህዝብ የተሰወረ ነገር እንዳለ ግምት የሚያስፈጥር ነው። ታዲያ ህሊናቸውን የሚቆረቁራቸው ከሆነ፤ እስኪያቾ ቅጽበት ድረስ አቆይተው አቡነ ማትያስ በሌሉበት ከመናገር ይልቅ፤ ሊጠይቁት የፈለጉትን መረጃ ለህዝብ አብራርተው፤ አቡነ ማትያስ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ለህዝብ መግለጽ አይገባቸውም ነበርን? አቶ አዲስ ማድረግ የሚገባቸው ሳያደርጉ፤ አቡነ ማትያስ በሌሉበት ይህን መናገር የእምነታቸውንና የጋዜጠኛነታቸውን ሃላፊነት ወደ አሉባልተኛነት መቀየር አይሆንባቸውምን? አቡነ ማትያስንስ ቢሆን በምናውቀውና በማስረጃ በተደገፈ ነገር ብቻ እንውቀሳቸው እንጅ፤ <u>አቶ አዲሱ ተጠራጥረው ባቀረቡት መንገድ አቡነ ማትያስን በጥርጥር መንቀፍ ክርስትናችን ይፈቅዳልን? እንደነዚህ የመሳሰሉትን እንክርዳድ ነክ መንፈሶች በህዝብ ጭንቅላት ላይ መርጨት ተገቢ አይደለምና ማቆም አለብን!</u> በዚህ ስብሰባ ላይ አቶ አዲሱ “እውነት ተምራችሁ እንድትሄዱ እፈልጋለሁ። ቀኖና ዶግማ ተጥሷል የተጣሰው ማርያምን የሚበጠብጡ ናቸው። ርዕሰ ደብር አብርሃም ስለ ዶ ግማው መጣስ ሊያስረዱ ይችላሉ” ሲሉ ለተሰበሰበው ህዝብ ተናግረዋል።

ራሳቸው አቶ አዲሱ አበበ ኅትተው ስላመጡት አነሳሁት እንጅ፤ በዚህ ጉዳይ ከራሳቸው ጋራ በወቅቱ ተነጋግረን <u>“አቡነ ማትያስ ወዳጇ ናቸው፤ ከሳቸው ጋራ እስከ መጨረሻ እሰለፋለሁ። እሳቸው ስላወገዙህ ያንተንም ቅስና አልቀበልም”</u> በማለታቸው ሳንግባባ ተለያየን። በገርነት ለነገረ መለኮቱ ቀናኢ በመሆናቸው ባልገባቸው ነገር ተቀያይመን ከመቅረት፤ እምነታችን በሚያዝዘው መሰረት ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ እና ሊቀ ማዕምራን ዶክተር አማረ ካሣዬ እንዲያስረዷቸው ፈልጌ፤ ከዲሲ እራሳቸው አቶ አዲሱ፣ ዶ ክተር አማረና ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ፤ ከከንሳስ ደግሞ የከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጸሐፊ እና እራሴ በሶሶት መስመር ተነጋግረን። ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ እና ዶ ክተር አማረ፤ <u>“አቡነ ማትያስ ቀሲስ አስተርአየን አወገዙኩ አላሉም። አቡነ ማትያስ አደረኩ ያሉት ግዚያዊ እገዳ ነው። እገዳውም ቢሆን በራሳቸው በአቡነ ማትያስ እውቀት ጉድለት እንዳደረጉት፤ በቅዱሳት መጻህፍት እና በአኀት አብያተ ክርስቲያናት ጥናት ተደረስቦት፤</u>

የቀሲስ አስተርአየ እምነትና አቋም ትክክል እንደሆነ ተረጋግጦ በተላለፈው ውሳኔ ነፍሳቸውን ይማርና አቡነ ይስሀቅ እገዳው መነሳቱን ለሚመለከተው ሁሉ በጽሁፍ ገልጸውታል። አንተ ከየት ፈጥረህ ነው የምታወራው?" በማለት በተግሳጽ ነግረዋቸው፤ ያሰራጩት የነበረው አሉባልታ እንደሆነ ተረድተው አቶ አዲሱ ይቅርታ ጠይቀውበት አልፏል። በወቅቱ የተነሳውን ጉዳይ በተመለከተና በቀሲስ አስተርአየ ላይ ስለተነሳው ዝርዝር ለማወቅ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ።

- [ አቡነ ማትያስ በቀሲስ አስተርአየ ላይ የጻፉት ጊዚያዊ የእገዳ ደበዳቤ እና ጊዚያዊ እገዳዉ የተነሳበት ደብዳቤ የሚቀጥለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ። የአቡነ ይስሐቅ ደብዳቤ ]።
- እንዲሁም እኅት አብያተ ክርስቲያናት የሰጡትን ምስክርነት ዝርዝር የሚቀጥሉትን ሰንሰለቶች በመጫን ያንብቡ :-
  - የግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን
  - የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን
  - የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን

በወቅቱ ራሳቸው ይቅርታ በመጠየቃቸው የታለፈውን ነገር፤ አሁን በሌላ ጥያቄ አጥብቂኝ ውስጥ ሲገቡ "የናንተን ችግር እንፈታለን የሚሉ ማርያምን የሚበጠብጡ ናቸው" የቀኖናን የነገረ መለኮት ከሆነ "እኛም ጋ ቀኖና ዶክትሪን ተጥሷል" ብለው እንዲያውም "በዶ ክተር አማረ ላይ ጥያቄ አለኝ" በማለታቸው ሽፍጣቸውን በራሳቸው መሰከሩ። የቅድስት ማርያም አስተዳዳሪ ዶክተር አማረና፤ የቅድስት ማርያም ቦርድ ጸሐፊ ሆነው በማገልገላይ ያሉት ወይዘሮ ወሰን፤ በጓደኛቸው ታደሰ ላይ በተወደሰው መንፈሳዊ ጉባዔ ላይ በመገኘታቸው እጅግ መበሳጨታቸውንም አጉልተው ከማሳየታቸው በቀር የተናገሩት ፍጹም ሽፍጥ ነው።

ከሁሉም ይልቅ "ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት" በሚል ርእስ በጠለሰሙት፡ ክህደት ያስተማሩትንና በሌላም ጠባያቸው የዋሸንግተን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዳባረረቻቸው እያወቁ፤ ያስተዳደር ቦ ርዱን ለመክሰስ በሰበሰቡት ጉባዔ ፊት "ቀኖና ለመፍረሱ ርዕሰ ደብር አብርሃም ሊነግሩን ይችላሉ" ብለው ለምስክርነትና ለነገረ መለኮት አስረጅ አድርገው ማቅረባቸው ነገሩን የሚያውቀውን ሁሉ ያቶ አዲሱ ሁኔታ አስገርሚል።

ባላሰበውና ባልተዘጋጀበት ነገር፤ ባንድ ሰው ላይ አንድ ነገር ድንገት ወርውሮ ማስደንገጥ ቅስናየና ያደኩበት ባህሌ ስለማይፈቅዱልኝ፤ ይህችን ጦማር በመዘጋጀት ላይ ሳለሁ፤ ስማቸውን እየጠራሁ ለመጻፍ መዘጋጄቴን ለአቶ አዲሱ በስልክ በነገርኳቸው ጊዜ፤ አቶ አዲሱ "በኔ ላይ አተኩረህ ከምትጽፍ ይልቅ በVOA ላይ ብትጽፍ ለውጥ ሊያስከትል ይችላልና። በዚህ ጉዳይ ባልደረቦቼን አነጋግር ብለውኝ፤ የወይዘሮ ትዝታ በላቸውንና ያቶ ንጉሤ መንገሻን ስልክ በሰጡኝ ጊዜ፤ *"ቀኖና ለመፍረሱ ርዕሰ ደብር አብርሃም ሊነግሩን ይችላሉ"* ማለታቸው ህሊናየን ትኮሰኩሰኝ ስለነበረ፤ ህሊናየን ለማጽዳት እድል ገጠመኝ። "ቀኖና ለመፍረሱ ርዕሰ ደብር አብርሃም ሊነግሩን ይችላሉ" የሚለውን ሰምቻለሁ። ለምን ይህን አደረጉ ? ስላቸው የሰጡኝ መልስ *"ሌላ ሰው ስለጠፋ ነው"* የሚል ነው። ይህን ለኔ የነገሩኝ ቃል ለራሳቸው ለርእሰ ደብር አብርሃም "ሰው ስለጠፋ አንተን ጋበዝኩሁ" የሚሉ አይመስለኝም።

በሁሉም ዙሪያ አቶ አዲሱ አበበን የተረዳኋቸው፤ ህሰትን ማስመሰልን ሽፍጥን ለማራቅ ሰይፊ ነበልባል የሆነችውን የጋዜጠኝነት ሙያ፤ የግል ወዳጅ ማብዣ የጠሉትን መጉኛ። የዳቦ ማብስያ የብረት ምጣድ በማድረግ ዳቧቸውን እያበሰሉ እውነትን እያሳረሩ ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የእውነት ፋናዋ እንዲጠፋ ሀሰት እንድትሰፍን ሁሉንም ጋርደው በመሸፈን ተርገብጋቢ ቆጽለ በለስ ሆነው አየኋቸው።

እንግዲህ አቶ አዲሱን ራሳቸው በሚያደርጉትና በሚነገሩን ስንመዝናቸው፤ በቨርጅንያ የተከሰተው ነገር ለህዝብ ለመግለጽ የ VOA መመሪያ የሚያፍን እንደሆነ ለመቀበል እጅግ አዳጋች ይሆናል። "ለፕሮግራም የሚሆን ነገር አይደለም። VOA የራሱ አሰራር አለው" እያሉ የሚነግሩንን አምነን መቀበል ሞኝነት አይሆንምን? በነ አባ ፋኑዔል የሚካሄደውን ያዩትንና የተገነዘቡትን ላለቃቸው አቅርበው፤ አለቃቸው የታደሰና ያባ መላኩ ጉዳይ የጓደኞችህ ጉዳይ ነውና ሽፍነው ደብቀው አታውጣው ማለታቸውንና አለማለታቸውን በመጠየቅ ልንደርስበት አንችልምን?

አሁንም ለአጽንኦተ ነገር እደግመዋለሁ ! አቶ አዲሱ ሳይሸፍኑ ላለቃቸው ጉዳዩን ገልጸው አቅርበውት፤ አለቃቸው ለህዝብ አታቅርብ ይሏቸዋል ብለን መገመት ያስቸግራል። ራሳቸው አቶ አዲሱ በሙያቸው ለህዝብ ግልጽ እንዲሆን ለvoa አቅርበውት፤ voa ለህዝብ እንዳያቀርቡት ቢከለክላቸውም እንኳ፤ ባለባቸው የሞራል ግዴት፤ መከልከላቸውን መረጃ ለሚፈልገው ህዝብ ገልጸው ድርጅቱን መልቀቅ ነበረባቸው።

ከላይ አጠንክሬ እንደተናገርኩት፤ ይህችን ጽሑፍ ያቀረብኳት፤ አቶ አዲሱ ከላይ የተገለጸውን አምነው የሚቀበሉት ከሆነ ህዝቤንም ሙያየንም አምላኬንም በድያለሁ ብለው ንስሀ በመግባት ሰይፈ ነበልባል ጋዜጠኛ ሆነው ቤተ ክርስቲያናቸውንና ህዝባቸውን እንዲያገለግሉ እንጅ ለመጉዳት አይደለም። ናታን በነበልባላዊት ተልእኮው ዳዊትን አንቆ ይዞ "እግዚአብሔርን በድያለሁ" አሰኝቶ ወደ ትክከለኛ ሕሊናው እንደመለሰው፤ አቶ አዲሱም ጓደኞቻቸውን እንደነ አባ ፋኑዔል የመሳሰሉት ሰዎች ሸፍነው ከማያዝ ይልቅ፤ በመጀመሪያ እሳቸው ወደራሳቸው ህሊና ተመልሰው፤ ሰይፈ ነበልባል ጋዜጠኛ መካሪ ገሳጭና ጠጋኝ በመሆን፤ በኃጢአታቸው የገረፋትን አንቀው ይዘው ልቡናቸውን በንስሀ እየሰበሩ "እግዚአብሔር ኃጢአትህን አርቆልህል አትሞትም" እያሉ ወደ ትክከለኛው ህሊናቸው እንዲመለሱ መርዳት የሚችሉ ሰይፈ ነበልባል ጋዜጠኛ እንዲሆኑ ነው።

በተረፈ፦አቶ አዲሱ አበበ ከጓደኛቸው ከነ አባ ፋኑዔል ጋራ ያላቸውን የግል ጠንካራ አቋም በህዝብ ጭንቅላት ለመክተት ባደረጉት ሙከራ፤ "መሪዎች ወደ ትክክለኛ ህሊና እስኪመጡ ድረስ የትም ባለመሄድ ምእመናን እንደኔ አቋም ቢወስዱ ይሻላቸዋል" ብለው እንደሰበኩ፤ ክርስቲያን ጋዜጠኞች እና ሁላችን ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንም፤ አቶ አዲሱ አበበ ወደ ክርስቲያን ጋዜጠኝነት ሙያቸው ተመልሰው ሰይፈ ነበልባል ጋዜጠኛ መሆን እስኪችሉ ድረስ፤ ለመምከር አቋም ብንወስድ ለሳቸውም ለኛም የተሻለ እንደሚሆን ምኞቴን በመግለጽ ሀሳቤን እደመድማለሁ።

ይቆየን።

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::
http://www.medhanialemeotcks.org/